# በሚኒሶታ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር

*ቢቻል መተባበር ካልሆነም መከባበር*

***በሚኒሶታ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር በኢትዮጵያ የሚካሄደዉን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በቅርብ ከሚከታተሉ አቻ ማህበራት አንዱ ነው።***

*በ1997 የቅንጂት መሰረት የሆነው መኢአድ ፡ ምንም እንኳን በወቅቱ ለድል በቀቶ ህዝብ በምርጫ የሰጠዉን ስልጣን በአምባገነኖች ቢነጠቅም ፡ ሰፊ ህዝባዊ መሰረት እና ድጋፍ ያለዉ መሆኑን ማሳየት የቻለ ፓርቲ ነዉ።*

*መኢአድ ሲወጠን በሂደትና አሁንም እየተከተለ ያለዉ የፖለቲካ መሰመር በፍጹም የኢትዮጵያ አንድ አገርነትና ሉአላዊነት ተመስርቶ ለእያንዳንዱ የግል ነፃነት ለኢትዮጵያዊነት ክብር እና ኩራት የታገለ እና በመታገልም ላይ ያለ በተለይም ኢትዮጲያ የነበረች ያለችና ወደፊትም የምትኖር መሆኑዋን በማያሻማ መልክ በፐሮግራሙ የደነገገ ፓርቲ ነው።*

*መኢአድ በተለይም መሪው ምን ግዜም በማይለወጥ አቅማቸው ኢትዮጵያዉያን አክብሮትንና አድናቆትን ሲቸሯችው በተቃራኒዉ ወያኔዎች ፡በቋንቋዋ ቡድን የዘር ፖለቲካን የሚያራምዱ እና የውጭ ሃይሎች እንደ “ግትር” ፖለቲከኛ ይቆጥሯችዋል።ሆኖም ፓርቲው ከአቋዋሙ ፈቀቅ ሳይል ትግሉን ቀጥሎበታል።*

*የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ይህንን ትግል ሲያካሂድ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖለት አይደለም፤ ይልቁንም በዋናነት ከታጠቀ መንግስት ነኝ ባይ ወያኔ ጀምሮ የኢትዮጵያን ጥንካሬ ከማይፈልጉ የዉስጥና የዉጭ ሃይሎች ጭምር ያደረገውና በማድረግ ላይ ያለዉ ቆራጥ ሰላማዊ ትግል ፡የህይወት መስዋእትነትን የአካል ጉዳትን መታሰርን መሰደድን መራብና መዋከብን ጭምር ጠይቆታል። ለትግሉም አሰፈላጊ የሆነውን ሁሉ ከፍሎበታል፤አሁንም እየከፈለ ነው።*

ከሁሉም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን ትናንት መኢአድን ተጠግተው በቅንጅት ስም አብረው የተሰለፉ ሃይሎችና ጥቂት ደጋፊዎቻችው በፈጠሩት እና ሊፈጥሩ በሚሞክሩት ሁከት ትናንት ያጨናገፉትን ድል ዛሬም ውጤት እንዳያገኝ ሲባዝኑ መታየታቸው ነው።

ከሰሞኑመኢአድ ከገዥው የወያኔ ፓርቲ ጋር ባደረገው ድርድር እናበተፈራረመው የስነ ምግባር ስምምነት ላይ ተመስርቶ በውጭ አገር የሚገኙ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ አስተያየቶችን ሲሰነዝሩ ማህበራችን በጽሞና ተከታትሏል።

በተለያዩ ድረ ገጾች እና በአጠቃላይ የ ሳይበር ሚዲያ ከተጻፉ እና ከተደመጡ አስተያየቶች ጥቂቶች በሳል የፖለቲካ ድጋፎችን ከፊሎች ጨዋ አስተያየቶችን የሰነዘሩ ቢሆንም አንዳንዶቹ ግን በተራ አሉባልታና የስም ማጥፋት ዘመቻ ተደምጠው በማየታችን በጣም አዝነናል።

ለመሆኑ ስድብ ኢትዮጵያዊ ባህል ነው? የኢትዮጵያን ህዝብ ከወያኔ ነጻ ለማውጣት በመደረግ ላይ ላለው የፖለቲካ ትግልስ ምን አስተዋጽኦ ይኖረዋል?

ይነሰም ይብዛም መኢአድ የሚያደርገውን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማደናቀፍ መሯሯጥ ማንን ለመጥቀም ታስቦ ነው?

መልሱን በዚህ ረገድ ለተሰማሩ እንተውና በእኛ በኩል ግን “በ ፖለቲካ ጨዋታው ሜዳ ላይ ያሉትን የወገን ቡድን ተጨዋቾች መሳደብና ማዋረድ ድሉ ለጠላት እንዲሆን ከመመኘት የሚመነጭ ነው” እንላለን። ይህንን አሌ የሚሉ ካሉ በጸያፍ ቋንቋቸው እና ስድባቸው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዴት እንደሚጠቀም ያብራሩልን።

የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ከተጋረጠበት መከራ ነጻ ሊወጣ የሚችለው በራሱ በህዝቡ ትግል ብቻ ነው። ያንን ትግል ከዳር ለማድረስ ደግሞ ተደራጅቶ የሚያደራጀው ፡ታግሎ የሚያታግለው ፓርቲና መሪ ያስፈልገዋል። አሁን በኢትዮጵያ ከሚታዩ እንቅስቃሴዎች መሃከልም ማን ለሱ መቆሙን ጠንቅቆ ያውቃል። የህዝቡን አዋቂነት ለሚጠራጠሩ ምርጫ 97ትን ያስታውሶአል ።

አሁን በኢትዮጵያ ከሚታዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወያኔ የአንበሳውንድርሻ ይዞ በጠሩ በገንዘቡ እና በጉልበቱ ተመክቶ ህዝቡን ላለፉት አምስት አመታት በችግሩና በረሃቡ በማስቃየት እና በማስፈራራትና የግድ አባል ሆኖ እንዲመዘገብ በማድረግ በ 2002 ባትመርጡኝ ስራም ንግድም ትምህርትም የእርዳታ እህልም ምንም የለም በማለት ላይ ነው። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው የመኢአድ መሪዎችና አደራጆች ህዝቡን በመስዋእትነት ያደራጁት። ወያኔ በአደባባይ ከሚያደርገው በተጨማሪ በራሱ የተፈጠሩ “ተቃዋሚዎች” በአካሄድ ለየት ያሉ መሰለው በግብ ግን አንድ ሆነው የሚሰሩም እንዳሉ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ትናንት ከቅንጅት አፈንግጠው ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ነን ብለው ያወጁት ደግሞ ውለው ሳያድሩ ርስ በራሳቸው ተከፋፍለው ከመባላት ሌላ ምንም ፋይዳ ያለውስራ ሲሰሩ አልተመለከትንም። ይልቁንም በቁዋንቁዋ ቡድን ከተደራጁ የጎሳ ፖለቲከኞቸ ጋር አብረው ኢትዮጵያን መጀመሪያ አፍርሰው እንደገና ሊገነቡልን ሸር ጉድ ማለታቸዉን አብረዋቸው የነበሩ ይመሰክሩባቸዋል።

የሚገርመው ደግሞ በኢትዮጵያ ሰው የጠፋ ይመስል ትናንት ኤርትራን ካስገነጠሉ አገሪቱን ወደብ አልባ ካደረጉ የዘር ፖለቲካን ካራመዱ እና በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ካፈራረሱ ወያኔዎች ጋር እየሰሩ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት መድከማቸውን ይነግሩናል።

ዛሬ አብረዋቸው የተሰለፉት ወያኔዎች ራሳችው ወንጀለኛ መሆናቸዉን እየነገሩን እና እየነገሩዋቸው በፓርቲያቸው ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ አባል በማድረጋቸው ሌላው ቢቀር ህዝቡ ምን ይለናል አይሉም? ለመሆኑ በውስጣቸው መቻቻል ጠፍቶ ከአባረሩዋቸው ጋር መደራደር ያልቻሉ ከወያኔዎች ጋር የሚያስማማ ምን አይነት መርህ ነው?እኛን የሚገባን ግን ወንጀለኛ በተያዘ ጊዜ ለ ፍርድ ይቀርባል እንጅ አይሾምም።ለዚህም ነው የናዚ ወንጀለኞች አሁን ድረስ የሚሳደዱት፡በሩዋንዳ በኮንጎ በሱዳን በሰርቢያ እና በሌሎችም አገሮች ያሉ በህዝብ ላይ ሰቆቃ የፈጸሙ ሁሉ አሁንም ተፈላጊዎችና ተጠያቂዎች ናቸው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ አሁን በሰልጣን ላይ ያሉትም ሆኑ እንደገና እንዲመሩን በአንድነት የታጩልን ወያኔዎች ፍርድ ተጠባባቂ ወንጀለኞች ናቸው።

በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ ውጭ ሆነው ትግል እናካሂዳለን የሚሉ ወገኖችም መኖራችውን እናውቃለን እንዴትነቱን እና መቼነቱን ባንረዳም በኢትዮጵያ አንድነትና በጸረ ወያኔነት እስከተሰለፉ ድረስ መብታቸው ነው። በአንጻሩ የሰላሙ ትግል አብቅቶለታል የሚያዋጣው የትጥቅ ትግል ነው የሚለውን የሚያራምዱም አልታጡም ፤ምን ውጤት ላይ እንደደረሱ ባንሰማም የኢትዮጵያ ህዝብ ከህወሃት ዘረኛ አገዛዝ ለመላቀቅ የትኛውንም መንገድ ቢከትል የግል ምርጫው ነው።

መኢአድ በምርጫ ዘጠና ሰባት ያገኘውን ልምድ እና የ ሰራውን "ስህተት" መርምሮ የጀመረውን ትግል ከግብ ሊያደርስ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል በአገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት መሃከል እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ነው ሰንል ከልብ በመነጨ እምነት ነው።

በተለይም የመኢአድ መሪ ክቡር ኢንጅኔር ሃይሉ ሻውል በአሜሪካ ቆይታቸው ህክምናቸዉን አጠናቀው ከሆስፒታል በወጡ ማግስት ጀምሮ የትግል ስራቸውን ለመቀጠላቸው የሚኒሶታ ደጋፊዎቻቸው የቅርብ ምስክሮች ነን።

መሪው ወደኢትዮጵያም ከተመለሱ በሗላ ህጋዊ በሆነ መንገድ የ ቅንጅትን ሰምና አርማ ለማስመለስ ጥረት ቢያደርጉም ፍትህ የለምና አልተሳካላቸውም።ሆኖም ወያኔ ሲሰማው የሚያስበረግገውን ሰምና ሲያየው የሚያስደነብረዉን የቅንጅት ምልክት ለነማን እንደሰጠው ይታወሳል።ዛሬ የዚያ ሰምና አርማ ወራሾች በምንሁኔታ ተቃዋሚና ተደራዳሪ እንደሆኑ ወደፊት የምናየው ይሆናል። እስከዚያው ግን እኛን የሚገባን በኢትዮጵያ ብቸኛውና እውነተኛው ተቃዋሚ ፓርቲ መኢአድ እና መሪውም ሃይሉ ሻውል መሆናቸውን ነው።

መኢአድ ባለፉት አመታት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክልሎች የነበሩት ጽ/ቤቶች የቅንጅትን መፍረስ ተከትሎ ተዘግቶበት እንደነበረ.ይታወሳል፡ሆኖምመሪውከተመለሱ ማግስት ጀምረው ከረዳቶቻቸው ጋር በመሆን ተሰፋ የቆረጡትን ታጋዮች አበረታተውና አዲሶችንም ጨምረው ጽ/ቤቶችን ለመክፈትና ህዝቡን እንደገና ለማደራጀት በተደረገው ግብ ግብ የመኢአድ አደራጆችና ተከታዮቻቸው የህይወትእና የአካል መሰዋእትነትን ከፍለዋል፣ ለእስር ተዳርገዋል ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ታዲያ ይህን ላደረጉ መሪና መላዉን የመኢአድ ታጋዮች በምስጋና ፋንታ መሳደብ ተገቢ ነው? ነፍሱን በገነት ያኑርልን እና በአንድ ድርሰቱ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን "ቃል የእምነት እዳ እንጅ የእናት የአባት እኮ አይደለም" ብሎ ነበር ለመኢአድ መሪዎች ግን ለኢትዮጵያ ህዝብ የገቡት ቃል ከእምነት እዳ በላይ ሆኖባቸው መከራ በተቀበሉ ምስጋናው ቢቀርባቸው ሊሰደቡ ግን አይገባም።ነውር ነው።

የየትኛውም አገር አምባ ገነኖች "ሺርፍራፊም" ቢሆን ለህዝብ መብት የሚሰጡትአስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው እንጅ በደግነትና በፈቃዳቸው አይደለም። መኢአድ እና ሁለቱ "ተቃዋሚዎች" ከወያኔ ፓርቲ ጋር ያደረጉት የሰነምግባር ደንብ ድርድርና ውጤቱም በህዝብ ትግል መሰዋእትነትና አስገዳጅነት የተገኘ እንጅ የወያኔ ቸርነት አይደለም። በአንድ በኩል ወያኔ ይሄንን በማድረጉበአንድ ወገን ለሰላም የቆመ በመምሰል ህዝብን ለማወናበድ ሊጠቀምበት ሲሆንበሌላ በኩል ደግሞ ፍርፋሪ ለሚጥሉለት ምእራባውያን መንግስታት የዲሞክራሲ ባህል አራማጅ መስሎ ለመታየት የሚሞክርበት ዘዴ ነው ። በሌላም በኩል

መኢአድ በበኩሉ የተገኘውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ያልተምዋላም ቢሆን ህዝብን ለማደራጀትና ለማታገልም ይጠቀምበታል የታሰሩ ታጋዮቹን ያስፈታበታል ወዘተ.ወያኔ የፈረመውን ሰነድ አፍርሶም ሲገኝ ህዝብ ያነሳሳበታል ለሰላማዊ አመጽ መንገድ ያገኝበታል።

ታዲያ ምኑ ላይ ነው የመኢአድ መደራደር ጥፋቱ? አንዳንድ ወገኖች በዚህ አይነት መደራደር መፈራረምና መጨባበጥ እንዲያዉም ወደ ምርጫ መግባትጭምር ለወያኔ ህጋዊ ሽፋን ስለሚሰጠው እንደሚቃወሙ ይነግሩናል።

እነኚህ ወገኖች ያልተረዱት ብዙ ነገር እንዳለ ይሰማናል። ለመሆኑ ወያኔ መቼ ነው ህግ አክብሮና ፈርቶ የሚያውቀው?በሌላም በኩል ለምእራባውያን ስለ ማጋለጥም ያነሳሉ፣መልካም፤ ሆኖም ወያኔን ለስልጣን ያበቁት ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም የምእራባውያንን መንግስታት አስተዋጽኦ ይዘነጋሉ። ያም ይቅር ለመሆኑወያኔ በ18 አመታት የመንግስትነት ስልጣኑ በኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመዉን በደል ተቀነባብሮ የምንሰማው ከነርሱ መስሎን ታዲያስ ጎበዝ ምን አደረጉልን? በ1997 በተደረገው ምርጫ ውዝግብ በአግአዚ ወያኔ ያለቁትን ህጻናት ወጣቶች እና አዛውንት፣በየእስር ቤቱ የታጎሩትን እና አሁንም የሚሰቃዩትን ምእራባውያን መንግታት አልሰሙ ይሆን?ታዲያ ምን አደረጉልን?ነገስ ምን እንዲደረግልን ነው የምንጠብቀው? እኛስ እርስ በርስ ከመባላት ውጭ ምን ቁም ነገር ሰራን? ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ በበደለ ቁጥር የአለም ባንክ አይ እም እፍ እና የምእራብ መንግስታት ገንዘብ በብድርና በእርዳታ ሲሰጡት ቢያንስ የኛም የታክስ ገንዘብ አለበት ብለን ሰንቶቻችን ለመቃወም ወጣን?

ታዲያ ይሄ ሁሉ እየታወቀ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ትግል የሚመራውን መኢአድን እና መሪውን ምን አድርጉ ነው የምንላቸው?ለእኛ እስገሚገባን ድረስ መደራደር የሰላማዊ ትግል አንድ አካል ነው። ተደራድሮ የተወሰነ ነግር ማግኘት መቻልም ሌላ ድል ነው። ሃይሉ እና መለስ ተጨባበጡ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት በ “ቅንነት” ለተሳሳቱ ለአቶ ሃይሉ ያላቸዉን ክብር እና ለመለስ ያላቸውን ጥላቻ በአለመብሰላቸው አሳይተዋል።ጉዳዩ ግን ከዚህ የዘለለና የተቀነባበረ የወያኔ የራሱ ተንኮል ነው፣ ምክንያቱም መኢአድን እና መሪዉን በዚህ መንገድ ካጥላላሁ እና የወያኔ ደጋፊ አስመሰዬ ማቅረብ ከቻልኩ ህዝብ አይመርጣቸውም በሚል ስሌት መንቀሳቀሱን ለመገመት የፖለቲካ ጠቢብነትን አይጠይቅም። ምርጫ ዘጠና ሰባትን ያስታውሱ።

አቶ ሃይሉ እና አቶ መለስ ሲጨባበጡ እኮ ሁለቱም ወገኖች የየሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው መሆኑን መገንዘብ እንዴት ይሳነናል? በአንድ ወቅት የአሜሪካው

ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ከቬኒዙዌላው መሪ ጋር ከተነጋግሩ በሁዋላ ጋዜጠኞች ይህንኑ አስመልክተው የርስዎ ሻቬዝን መጨበጥ የአሜሪካንን ጥቅም አይጎዳም ወይ ሲሉ ላቀረቡላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልሰውላችዋል።

"'IT IS UNLIKELY THAT AS A CONSEQENCE OF ME SHAKING HANDS OR HAVING a polite CONVERSATION WITH MR.CHAVEZ THAT WE ARE ENDANGERING THE STRATEGIC INTERESTS OF THE UNITED STATES"

BARACK OBAMA

ታድያ ነብዩ በአገሩ አይከበርም ሆኖ ተቸገርን እንጅ የኛም መሪ ሃይሉ ሻውል በድርድሩ የፊርማ ስነ ስርአት ላይ የሚከተለዉን ተናግረዋል።

"ይሄ እኮ አሁን እኛ የምንነጋገርበት ፤በጎሪጥ የምንተያይበት ስልጣን የህዝብ ነው እኮ፤ ያ ህዝብ ስልጣኑን እንዲወስድ ብለን ነው የምንለፋው...........

ብዙ ሰው ምን አንድ ኮድ ቢሟላ ምንድን ነው የሚል አለ። አንድ ኮድ እኮ አንድ ዲሲፕሊን ማለት ነው። አንድ መሄጃ መንገድ ማለት ነው። አንድ የእድገት መስመር ማለት ነው። ከዚህ በሗላ አለቀ ደቀቀ ብለን የምንዘጋው ምእራፍ አይደለም"

ሃይሉ ሻውል

ታድያ አላማን ሳይስቱ በሰላም መነጋገርን ባራክ ኦባማ ሲሉት ልክ የኛው ሃይሉ ሻውል ሲናገሩት ስህተት ይሆን?በቅንነት የተሳሳታችሁ ፍርድ ሥጡ።

በኢትዮጵያ ጥናት ጉዳዩ ተመራማሪ እና አለም አቀፍ ሊቅ የሆኑት ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ በዚሁ የድርድር ጉዳዩ ባቀረቡት አንድ ጽሁፋቸው ታሪክ ጠቅሰውየሚከተለዉን አስተምረዉናል።

"አቶ ሃይሉ እና አቶ መለስ ሲጨባበጡ አይቶ ኡኡየሚል ከክርስቶስ ልደት በፊት የጀመረ ጠላትነትን የወረሱት የ እስራእሉ ምናሄም ቤገን እና የፍልስጥእሙ ያስር አራፋት ሲጨባበጡ ያላየ ነው"

ጌታቸው ሀይሌ

በአጠቃላይ የሚኒሶታ ቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበራችን ለመሪው ለኢንጅኔር ሃይሉ ሻውል እና በየደረጃው ላሉ የአመራር አባላት ፤ ለሁሉም ታጋዮች

*አባላት እና ደጋፊዎች ያለንን አክብሮት ስንገልጽ ዛሬም እንደ ትናንቱ አብረናችሁ መቆማችንን በማረጋገጥ ነው።*

*ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ /*